# ዑነትና ንጋት እያደረ ይጠራል

ክፍል ሦስት

ወቅታዊ የኢትዮጵያ ሁኔታና _ የወቅቱ መሪ ተዋንያን

ዘመንፈስ ቢያድግልኝ

በክፍል አንድና ሁለት ልደተ ህዋሃትና የፖለቲካ ስንክሳሩ እንዴትና በምን መንገድና ስልት “ይውጋህ ብሎ ይማርህ” ዘዴ አሁን ኢትዮጵያ ላለችበት ሁኔታ ያጠመዱት ስውር ሴራ ከትምህርት ቤት እስከ ምንሊክ ቤተመንግሥት ብሎም ወደ መቀሌ ማቅናት ለማሳየት ሞክሪያለሁ። ይህም ሙትን ለመወቀስ ሳይሆን ለመደገፊም ለመቃወምም በዕውቅት ላይ የተመሰረተ ቢሆን ለራስ፣ለወገን ከዚያም ለሀገር ይጠቅማል በሚል ህሳቤ ነው።

ማንም ያገባኛል የሚል ዜጋ ህዝብና ሃገርን ማስቀደም ካልቻለ የጊዜ ጉዳይ እንጂ እንድ ጥዋት ጤዛ የት እንድገባ ሳይታወቅ በኖ መቀረት ያለ ነው። ሩቅ ሳንሄድ በዚሁ በሀገራችን ባለፉት አርባ ዓመታት ብቻ አፈር አይንካን ያሉ “ፖልቲከኛ” ነኝ ያሉን፤ ቀና ብለህ ዓየህኝ ተብለን እስር ቤት የውረወሩን፤ በቆንጆ ሚስታችን ወይም በቆንጆ ሴት ልጃችን በደለኛ ያርጉን፤ እነሱ የገቡበት መዝናኛ ወይም ሆቴል በመገኘታችን ከገልመጫ እስከዛቻ የደረስብን ሁሉ እንዝያ ሰዎች በምን ሁኔታ እንዳለፉ ካሉም ደገሞ ከስብዕና ወርደው የቁም ሞት ውስጥ መሆናቸው እያየን ነው። ያ በውሸት ሲሸነግሉትና ከጎረቤቱ፤ ከአብሮ አደጉ ያናከሱት ግን በአብሮነት ሕይወቱ እንድቀጠለ እያየን ነው።

በርግጥ ታሪክ መላልሶ እየተደገመ ስዎች ካለፈው መማር እያቃታቸው አልያም ሆድ አምላኩ እየሆኑ ካለፈ ከመማርና የተሻለ መላ እንደማብጀት ያንኑ መልክ እየቀያየሩ ይድገሙታል። አለማወቅ እንዳይባል ተምረናል ይላሉ፤ በተፈጠረች ደካማ ጎን እየገቡ የህዝቦችን ስላምና ፍቅር ያናጋሉ፤ ዛሬም በ21ኛው ክፍለ ዘመን አይት ቅድመ አያቶቻችን የጣሉትን የፍቅርና የአንድነት መሠረት ለማናጋት ይጥራሉ፤ ምንም እንኳ ከነዚህም በፊት መስል ድርጊት የሞከሩ በህዝብ ትዕግሥትና የስከነ መንፈስ እንዲሁም በደምና በዘርመል የተቆራኝ ሀይወት እንዳከሸፈው ሁሉ ይህ የጊዜው ሁኔታም ዕጣ ፈንታው ከዚህ ውጭ እንዳልሆነ ይህ ጸሃፊ ሙሉ ዕምነት አለው። ይሁንና ይህ ትውልድ ዕውነቱን ማውቅ ይኖርበታል አውቆም እንዲደግፍ አውቆም እንዲቃወም ጸሃፊው የሚያቀውን ያለፈበትን ዑነት ማካፈል የዜግነት ገዴታው ሆኖ ይሰማዋል።

በአሁኑ ሰዓት ህዋሃት በፈጠረው መንገድ ሁሉም እየተነሳ የብሄር ስም እየጠራ ፓርቲ ነኝ የጊዜው እንጉርጉሮ ሆኗል። በአለፈት 27 ዓመታት ከየቢሄረ ሰቡ ጥቂት የማይባሉ ህዝቡ መስማት የሚፈልገው እየተናገሩ ነገር ግን የሚፈልጉትን እንጂ ህዝቡ የሚፈልገው ሳይሰሩ የግል ጥቅም ሲያራሩጡ የነበሩ ጥቂት አይደሉም። ራሳቸውም ቤተሰቦቻቸውም ተጠቃሚ አድርገዋል። በዚህም የተነሳ ኢትዮጵያና ህዝቧ ሊሸከሙት ከሚችሉት በላይ በ”ፓርቲ” ተብዬ ተጥለቅልቃለች። ቢሆንም ይህ ጸሃፊ ማየት የሚፈልገው የኃላ የጎላ ታሪክ  ያላቸውና የዜና አውታሮችና ህዋሃት _ ኢሒአዲግ  በፈጠርዋቸው የተውሰኑ ግለ ሰብ ፖልቲከኞች ላይ እንጂ ለዕለት ጉርስ፣ለውጭ ቢዛና፣ለቤሳ ቤስቲ ሲሉ የፖለቲካ ካባ የደረቡትን አይደለም።

ከሁሉ በፊት ከእኔ ማነኝ መጀመር ግድ ይላል። ይህም ለግል ዝና ሳይሆን በመጀመርያ የምናገርለት ማኅበረ ስብ ምንነትና ታሪክ በማውቅ ይጀመራል። እኔ አውቃሎህ ብሎ መጀመር ትዕዝብት ላይ ከመጣሉ በላይ ራስንም ሌላው ወገንም ሊጎዳ ይችላል። አባቶቻችን ያስተማሩን መስዋዕት ከፍሎ ሌላውን ማዳንና ብርሁ ተስፋ መፈንጠቅ እንጂ በሌላው ሞትና ስቃይ የራስን ጎጆ መቀለስ አይደለም። ዛሬ ተጠዋሪ ሆነው የምናያቸው አባቶች እንደ ዘመነኛው “ፖለቲከኛ” ተብየ በሌላው መስውዕትነት ለመኖር ሽርጉድ ባለማለታቸው ነው። ይህን ራስን ለሌላው የመሰዋት ቁርጠኝነት ርቆን ከሄደ ውሎ አድራል። በተለይ ከ1983 ዓም በኃላ።

ወደ ዋናው ርዕሰ ጉዳይ ስመለስ በኢትዮጵያ ከዘመነ መሳፍንት በኃላና አህዳዊ መንግሥት ከቆመ ወዲህ ዘመናዊ ፖለቲካዊ ዕንቅስቃሴ ተጀመረ የሚባለው በጎጃም፣በባሌና በትግራይ የታዩ በአርሶ አድሮች የተነሱ የፍትህና የግብር በዛብን ጥያቄዎች ሲሆኑ ጎልተው በአደባባይ የወጡትም በጀነራል መንግስቱና በውንድማቸው ግርማሜ ንዋይ የተሞከረው የ1953 በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር መፈንቅለ መንግሥት ነው። በርግጥ እዚህም እዛም በግለስብ ደረጃ አሻፈርኝ ያሉ መስለሎቻቸውን እያስከተሉ ያመጹ አልነበሩም ማለት ግን አይደለም።

በሌላ በኩልም የአካባቢያቸውን ሁኔታ ለመቀየርና ለመለውጥ በተለያዩ የማኅበርስብ ግልጋሎት እየተደራጁ የታገሉ በዙዎች ናቸው። ከነዚህም የጉራጌ ልማት ማኅበርና የሜጫና ቱሉማ ራስ አገዝ ማኅበር በግንባር ቀደም ይነሳሉ። የሜጫና ቱሉማ ማኅበር በርካታ የልማት ሥራ በማከናውን በኦሮሞው ማኅበረስብ ተቀባይነት ማግኘትና ከባሌ የአርሶ አድር ዕንቅስቃሴ ግኑኝነት አለው በሚል በውቅቱ የነበረው ገዥ መድብ ድርጅቱ  እንዲታገድና በአመራር ላይ የነበሩትንም በማሰሩ ጥቂት ከእስር ያመለጡ አብላቱ በቀጥታ ወደ ፖለቲካው መድርክ ተቀላቀሉ።

የማኅበሩ አብል የነበሩ አቶ ሁሴን ሶራ እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር በ1967 ከሀገር ሸሽተው ወ ደ ሶማልያ በመግባት ከሌሎች የኢትዮጵያውያን ስደተኞች በመሆን የመጀመርያው "የኢትዮጵያ ዜጎች ነጻ አውጪ ግንባር" መሰረቱ። ሁሴን ሶራም የመጀመርያው ዋና ጸሀፊ ሆነው ተሰየሙ። በዚህም በኢትዮጵያ ታሪክ የሃገሪቱን ነጻ አውጪ ደርጅት በማቋቋም ፈር ቀዳጅ ሆኑ። ምንም እንኳ የታሪክ ሻሞ ዑነቱን ቢያሽመሽመድውም በርካታ የኦሮሞ ተውላጅ ያልሆኑም በብዛት ነበሩበት። ከነዚህም እንደ ሻምበል ተገኝ ወርቁ የቀድሞ የፈጥኖ ደራሽ አባል የጉርጌ ተወላጅ፤ ንጋቱ ተሰማ የምንጃር ወረዳ ገዥ የነበሩ፤ አቶ ቢተው ቢልልኝ የጎጃም ተወላጅና  በአስብ ተፈሪ ነጋዴ የነበሩ ይገኙበታል።ይህው ድርጅትም "Ethiopian National Liberation Front (ENLF)" በመባል እንቅስቃሴው ቀጠለ። ሆኖም በሶማሊያ የነበረው ቆይታቸው በዚያድ ባሬ መንግሥት በብጎ ዓይን አልታየም። ይህም በሁለት ምክንያት ነበር አንደኛው የኢትዮጵያ ዜጎች የሚለው ስያሜ ለዛው ጊዜ የሶማሊያ መሪዎች የሚዋጥ አልነበረም፤ የነሱ የምዕራብ ሶማሊ ነጻ አውጪ ድርጅት ኦጋዴን ነጻ የማውጣት ዓላማ ሐረርን ባሌን ስለሚያጠቃልል እንደ ዕንቅፋት ይመለከትዋቸው ስለነበር፤ በሌላ በኩል በየመን የነበረው የኢትዮጵያ ስደተኛ ለመመለመል አመቺ ስላልነበረ ወደ የመን አመሩ።

በየመንም ምልመላው ቢሳካም ያስለጠንዋቸው ምለምሎች ወደኢትዮጵያ ለማስገባት በስሜን ሶማሊ በአቦ ጃራ አባ ጋዳ የተሞከርው ዕንቅስቃሴ በሶማሊያ የጸጥታ ኃይሎች ከሽፎ በዞዎች ወደ ለእስር ተዳረጉ። በሁለተኛው ሙከራቸው በከፊል ተሳክቶላቸው በጨርጨር ተራራዎች ለመንቀሳቀስ ቻሉ። በዚህ ጊዜ ነው ኢትዮጵያ የሚለው መጠርያቸው ኦሮሞ በሚል የተኩት። ጂን ፖል ሳርተር ትውልድ ሲቀየር አዲስ ዜማና ስነ ጥበብ ግድ ይላል

"every age has its own poetry; in every age the circumstances of history choose a nation, a race, a class to take up the torch of creating situations that can be expressed or transcended only through poetry." Jean – Paul Sartre

"እያንዳንዱ ትውልድ የራሱ ስነ ግጥም (ስነ ጥበብ) ይኖረዋል በየትውልዱ ያለው ነባራዊ ሁኔታ ሀገርን፤ ዘርንና ማኅብራዊ የመደብ ከፍፍልን የሚስቀጥል የብርሃን ችቦ የሚይዝ ይሻል ይህም በስነ ግጥም በአጠቃላይ በጥበብ ይገልጻል።" ጂን ፖል ሳርትር

በ1973 የቀዳማዊ ኃይልሥላሴ መንግሥት በወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት ሲወገድ ከስርና ከስደት ያመለጡ የሜጫ ቱሉማ አባላት ያድረጉት ጊዜው ጋር የሚሄድ ስነጥበብ ፈለጋ ነበር። ለእኔዚህም ነው በህቡዕ "ቀና በቀታ (Kena Bektaa)" ማለትም "አምባ ገነነት የሚቃወም የኦሮም ድምጽ" በሚል በራሪ ጽሁፍና ጋዜጣ ማሰርጨትና መቀስቀስ ተያይዘውት የነበረ። በ1973 የኦሮሞ አክቲቢስቶች ሁሴን ሶሮ, ኢልሞ ቂልቱ (Hussein Sora, Elemo Qiltu) ጨመሮ ሚስጥራዊ ስብሰባ በማከሄድ ለመጀመርያ ጊዜ በይፋ የኦሮሞ ነጻ አውጪ ድርጅት (ኦነግ) ሲቋቋም በዚሁ ስብሰባም የኦሮሞ ነጻ አውጪ ሰራዊትም (ኦለአ) _ Oromo Liberation Army or OLAም ይፋ ሆነ።

ነገሮች በዚህ ሁኔታ በመሄድ እያሉ በጨርጨር ተራሮች ይንቀሳቀስና በሀስን ኢብራሁም (እልሞ ቂልቶ) የሚመራው የኦነግ ሠራዊት አድማሱ ሲያስፋፋ ወታደራዊ መግሥት በጀነራል ጌታቸው ሺበሺ የሚመራ ጦር በመላክ የጭሮ ውግያ ተብሎ በሚጠራው ፍልምያ የጦሩ መሪዎች የነበሩት ሃስን ኢብራሂምና አህመድ ታሪክን ጨምሮ በርከት ያሉትን በመደምሰስ የነበረው ጦር እንዲበተን ተደረገ።

ይህን ተከትሎም በርካታ የኦሮሞ ተውላጆችና ከነሱ ተባበረዋል የተባሉ ሌሎችም እንገልትንና እስራት ደረሰባቸው። ከዚህ በኃላ በራሱ በድርጅቱ ወስጥም ከፍተኛ ሽኩቻ ተጀመረ። ምንም እንካ እንደ ህዋሃት ባይሰካም እዚህም የጎጥና የመንደር የበላይነት ለማስፈን በተደረገ የውስጥ ትግል በርከት ያለ የሕይወትና የአካል ጉዳት አስከፍሏል። እንዲህ እንዲህ እያለም ድርጅቱ መስነጣጠቅ ቢደርስበትምና በተለያዩ ጊዝያት በተለያዩ ቡድኖችና ግለ ስቦች የዓላማና የስትራትጂ መለዋወጥ ቢታይም "ኦነግ" የሚለው ስያሜ ግን ይዞ በመጋዝ ይገኛል።

በኢትዮጵያ በታዩት ፖለቲካዊ ዕንቅስቅሴዎች ኦነግ ተወደደም ተጠላም፤ ከኢሕአፓ፤ ከሜኤሶን፤ ከሌሎች ብቅ ጥልቅ ካሉትና አሻራቸው ጥለው ካለፉት ጭምር በተጽዕኖ ፈጣሪነት ተርታ ያስልፋዋል። የዚህ ጸሃፊ ዋናው ጉዳይ በድርጅቶች ወይም በግል የተንቀሳቀሱ ሰዎች ግላዊ ስብዕና ላይ ሳይሆን በአራመዱትና በሚያራምዱት አቋም ብቻ ስለሆነ በተቻለ መጠን አንባቢም በዚሁ አንጻር እንድሚመለከተው ተስፋ አለው። ስለ ኢሃአፓም ሆነ ስለ መኤሶን በውስጥ አውቂዎችም ሆነ በታሪክ ተሻሚዎች በዙ የተባለለት ስለሆነ መደጋገሙ አስፈላጊ አልመሰለኝም።

ኢሓዲግ ከግንባሩ አባል ድርጅቶች ጋር አሁንም ተጽዕኖ መፈጠሩ እንድሚቀጥል መዘንጋት አይገባም። ባለፉት 30 ዓመታት በሀገሪቱ በነብረው ፖለቲካዊ ሥልጣን ወደ መሬት የውረዱ የኔ የሚላቸው ፖሊስዎችና ስትራተጂዎች አሁንም በራሱ በኢሓዲግም ይሁን በሌላ ከመጠነኛ ማስተካከያዎች በቀር ሥር ነቀል ለወጥ መጠበቅ ወይም መሞከር እንደግመል ሽንት ወደ ኃሊት መሄድ ነው። ልብ ልንለው የሚገባ የግንባሩ  አባል ድርጅቶች መስራች አባላት በራሱ በህዋሃት፤ በአጋሩ በኢኤልፍ ከኢሓፓ፤ከኢድዩና ከቀድሞ የኢትዮጵያ ሠራዊት ምርኮኞች ቢሆኑም ከህዋሃት በስተቀር ባለፉት 30 ዓመታት የድርጅቶቹ ዴሞግራፊ እጅጉን መለወጡን ነው፤ ስለሆነም የኢሓዲግ ተጽዕኖ ፈጣሪነት እንዲህ በቀላሉ በፌስ ቡክ መዝሙር የሚገፉ

አይደለም። ምክንያቱም አማራጭ በሌለበት የኢትዮጵያ ፖለቲካ ምህዳር ከድጡ ወደማጡ እንዲሉ ከመሆን አያልፍምና፤ እዚህ ላይ ሚድያ ከወልዳቸው ያገራችን የጊዜው ተጽዕኖ ፈጣሪዎች አንዱ የሆነው ጁሀር መሐመድ ይህን አስመልክቶ ያስፈረውን ላስነበባቹ ወደድኩ..

*"In my view, keeping the current state, but changing the political process from one of domination and marginalization to one that fosters a pluralistic, inclusive and democratic coexistence holds the best advantage for the Oromo people and everyone else."*

*"በኔ አስተያየት ያለውን ሁኔታ እንዳለ ሆኖ ነገር ግን የፖለቲካ ሂደቱን ከአንድ ወገን የበላይነትና የማግለል ፖሊሲ ወጥቶ በብዛህነትን የተመሰርተና ሁሉን አቀፍ የሆነ የመቻቻል ዲሞክርስያዊ አስተዳደር ለኦሮሞ ህዝብ ሆነ ለሌላው ጠቃሚ ነው።" ይላል*

*ግን ጁሀር ማነው? ጁሀር በአሩሲና በሐረርጌ( በቀድሞ አጠራሩ ከፍላተ ሀገር) ድንበር በምትገኝ መንደር ከርስትያን እናቱና ከሞስሉም አብቱ የዛሬ 34 ውይም 35 ዓመት በፊት የተወለደ ኢትዮጵያዊ ነው። በልጅነቱ በአሰላ ለአንድ ዓመት  በካቶሊክ ትምህርት ቤት የተከታተል ሲሆን እዛው አሰላ በጭላሎ ከፍተኛ ሁለተኛ ትምህርት ቤት ትምህርቱን ቀጥሏል። በአዳማ (ናዝሬት) ቆይታውም የአስራ ሁለተኛ ቢሄራዊ ፈተናው ወስዳል። ። ከዛም በትምህርት ቤቱ ደጋፍ የከፍተኛ ትምህርት አግኝቶ ወደ ሲንጋፖር በማምራት ትምህርቱን ዩናይትድ ወርልድ ኮለጅ ኦፍ ሳውዝ ኢስት ኤሽያ ተከታትሏል። በዚህ ቆይታውም ይማርብት የነበረው ትምህርት ቤት ባለው ዓለም አቀፍ ግንኙነት ወደ አውሮፓና አሜሪካ የመጋዝ ዕድል አግኝቷል።*

*ከጊዜ በኃላም ወደ አሜሪካ በማቅናት  ስታንፎርድ ዩኒበርስቲ ቀጥሎም ኮሎምብያ ዩኒበርስቲም ገብቶ ተምሯል።* ከዚህ በኃላ ነው ስለ ኢትዮጵያ ብሎም ስለኦሮምያ ፖለቲካ ትኩርት መስጠት የጀመረው በለው የሚድያ ሰዎች ዘግበዋል። ጃሀር የፖለቲካ ጉዞ የጀመረው ነባሮቹ የኦነግ አመራሮች በመኮነን ነው። በሱ ዕምነት የኦሮሞ ህዝብን ፈላጎትና ትገሉን በድንብ አልመሩም ባይ ነው። ምንም እንኳ ሁሉም አልጋ በአልጋ ባይሆንለትም ለመጀመሪያ ጊዜ ሁስቡን በገልጽበት  "Failure to Deliver: The Journey of the Oromo Liberation Front in the Last Two Decades", በሚለው ጽሁፉ የኦነግ አመራሮችን ከፉኛ ነቀፈ። ወቅቱ ኦነግ ህዋሃት መር ከሆነው የሽግግር መንግሥት የወጣበትና በድርጅቱም መከፋፈልና ቅራኔ ጎልቶ የታየበት ስለነበረ በኦሮሞ ዳያስፖራ ተደማጭነትና ተቀባይነት ለማግኘት  በቃ።

የማኀበራዊ ሚድያ አጠቃቀም ችሎታው፤ ድፍረቱ፤ ውቅታዊ ጉዳዮች ላይ ለመደገፍም ሆነ ለመቃወም ፍጥነቱና ተከታዮቹ መስማት የሚፈልጉት ቢያምንበትም ባያምንበትም ጠንቅቆ በማውቁ  ለዕውቅናው አስተዋጻኦ አድርጎለታል። በርግጥ ከዕድሜውም ይሁን ከታሪክና ከፖለቲካ ዕውቀቱ ጥልቀት ውስንነት በሚያራምዳቸው አቋሞች የተከታይነት የወጥነት ችግር ይታይበታል። ለምሳሌ በቅርቡ የአዲስ አበባ መስተዳደር የኮንዶምኔም ዕጣ አውጣ በተባለ ጊዜ ወጣት ኦሮሞች በኛው መሬት የተሰራ ስለሆነ ለኛም ይገባናል ባሉ ወቅት ውድያው ባንዱ ስብሰባ በመገኘት እኛን ገድለው ካልሆነ አይገቡበትም ሲል ከጥቂት ቀናት በኃላ በዚሁ በአዲስ አበባ ጉዳይ ተያይዞ ስሙ እይተነሳ ያለው እስክንደር ነጋ ማስፈራራያና ዛቻ ደረስበት ሲባል እሱን የነካ እኔን የነካ ነው ሲል ተሰምታል። አዴፓ(ኦህዴድ) አንዳንድ መገለጫዎች ሲያውጣ ማብጠልጠልና አዴፓ ያዳንኩት እኔ ነኝ ሊያመሰግነኝ ይገባል ሲልም ተደምጧል።

በአድስ አበባ ዙርያ የተካሄደው የመሬት ወረራ የአርሶ አድር መፈናቀል በትግራይ በተለይ በእንደርታ አውራጃ የተጀመረ ቢሆንም እዛው የተሳካ መስሎ ስለታያቸው ህውሃት መር ኢሓዲግ የነደፈው  ስልት ለጃሃር ስፊና የተመቸ የትግል ነጻ አድባባይ ፈጥሮለታል። በዚህ መንገድ የተፈናቀለው የአከባቢው አርሶ አድር ልጅ በግምት ስም ለወላጆቹ አልያም ለራሱ የተሰጠቸው ሽርፍራፊ ሳንቲም ስታልቅ እንዳይሰራ የሞያ ከህሎቱ ከትውልድ ወደትውልድ የተላለፈው እርሻ እንጂ ሌላ ባለመሆኑ፤ እዳይርስና በወላጆቹ ፈለግ ሕይወቱ እንድይመራ መሬቱ

በመነጠቁ አውላላ ሜዳ ቀረ። በዕቅድ ታስቦበት ሳይሆን ትግራይ ወስጥ በኃይልና በእንግልት ያሳኩት በአዲስ አበባ ዙርያም ሲተገበር ጊዜው ጠብቆ ከእንጉርጉሮ ወደ አመጽ ሲያመራ ወጣቱ ጁሃር በተቀናጀ መልኩ ስለተጠቀመበት ህዋሃት መር ኢሃዲግን ጎሸ ተባርክ ብሎ መሪ ተዋናይ በመሆንና ጉዳዩን የአጠቃላይ የኦሮሞ ጥያቄ የትግል ዋልታና ማስባስብያ ለማደረግ አስቻለው። ይህ በሁኔታዎች የመጠቀም በቃቱ ከተጽዕኖ ፈጣሪዎች ተርታ አስልፎታል።

ያፈጠጠ ሃቅ መካድ አይቻልም ይህም በዚሁ ሁኔታው ቀጥሎ በኢትዮጵና እታገልለት አሎሁ፤ ብዙ ጥናት አርጌ በት አለሁ በሚለው የኦሮሞ ህዝብ ትግል ታሪክና ምንነት ከዕድሜ መብስል ጥልቅ ዕውቀት ካካበተ፤ ወፍዘራሽ ሙሁር ተብዬ ከሚያወሩት ከተላቀቀ በኢትዮጵያ በአጠቃላይ በኦሮም ትግል በተለይ የራሱን አሻራ ማኖር የሚችል መሆኑ ነው።

በሌላ በኩል ሌላው መገናኛ ብዙኃን የፈጠሩት ተጽዕኖ ፈጣሪ ስናይ እስክንደር ነጋን እንገኛለን። እዚህ ላይ እስክንደር አዲስ አበባ ተውልዶ፤ አድጎና ሳንፎርድ ተምሮ በአሜሪካ ትምህርቱ ተከታትሏል። እስክንድር ከአሜሪካ መልስ በቀጥታ ወደ ጋዜጠኝነት ይገባ ወይም ወደ ፖለቲካ ግልጽ አይደለም። ይሁንና በመላ አማራ ድርጅት በምክትል ሊቀመንበርነትና የውጭ ግኑኝነት ሃላፊ ሆኖ ግን ሰርቷል። የእስክንድር ስም ጎልቶ የተነሳው በ1997 በነበረው ህዝባዊ ንቅናቄ ያሳትማቸው በነበሩ ጋዜጦች ያስተላለፈው በነበር ምልዕክት በህዋሃት መር ኢሃዲግ ጥርስ ከገባ በኃላ ነው። በጊዜው በነበረው የፍትህ ሥርዓትም በሱና በቤተሰቡ ዕንግልትና እስር ደርሶበታል።በመጨረሻም በሽበርተኛነት ተከሶ ለበርካታ ዓምታት ለእስር ተዳርጎ ቆይቷል። ይበልጡኑ ግን ወደ መደረክ አጉልቶ ያወጣው የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፈ ብዙኃን መገናኛ ነው። ከነዚህም ጥቂቶቹ ብንመለከት ይህን ይመስላሉ።

*The Economist* magazine featured Eskinder Nega in its article titled "*the tightening noose on Ethiopia's press freedom*", at the end of September 2011, weeks after Eskinder's detention. Worse, it mentioned Eskinder Nega's newspapers as if exemplary ones..

ዘ ኢኮኖሚስት የተባለ ጋዜጣ እዘአ 2011 በወርሐ መስከረም "የሚድያ ነጻነት እይተኮልሸ ነው" በሚለው ዘገባው እስክንደር ለእስር ሲዳረግ "የእስክንድር ጋዜጣ" አንዱ ምስሌ ነውሲል አስፍሮልርታል

In December, CPJ (Committee to Protects Journalists) posted an article claiming '*it would be hard to find a better symbol of media repression in Africa than Eskinder Nega'*. CPJ's article portrayed Eskinder as a principled man who spent the last two decades defending human rights and currently facing an imminent death penalty.

በዚሁ ዓመት (2011) የጋዜጠኞች ተከላካይ ድርጅት (ሲፒጄ) በአስፈረው ጽሁፍ እንዲህ ብላል" በአፍሪካ ስለ ሚድያ አፍን ለማውራት ከእስክንድር ነጋ የበለጠ ምሳሌ አይገኝም።" ይልና ቀጥሎም "ባለፉት ሁለት አስር ዓመታት  በግንባር ቀደም ለስበዓዊ መብት ሲከራከር የነበር ሲሆን በአሁኑ ሰዓት አይቀሬ የሞት ፍርድ እይጠበቀ ነው።" ይላል

based on CPJ article, is the January 2012 article on the New York Times by Nicholas Kristof which claimed Eskinder could be suspected of none but advocating *free speech and the end of torture*.

የጋዜጠኞች መብት ተማጋች ያወጣውን መግለጫ መነሻ የኒዮርክ ታይምስ ጋዜጠኛ ኒኮላስ ከርስቶፍ እንዲህ በሎለታል "እስክንድር በምንም ሊከሰስ አይችልም ነገር ግን በነጻ ሃስብ የመግልጸ መብትና ማስቃየት እንዲቆም መማገቱ ካልሆነ"

በተጨማሪም ነገሩ

አደባባይ ቆሞ አበጀሁ ቢላችሁ፣

ይህን ባለ ጊዜ ምን ትሉታላችሁ፡፡ ሆነና

የነበረው ህዋሃት መር መንግሥታዊ መዋቅር በረባ ባልረባ ሲከሰው ሲያንገላታው ቆየ፣ በተለየም ደግሞ ከ1997 እስር በምህረት ከውጣ በኃላ አብረው ታስረው የነበሩ ጥቂቶቹ መልሰው ህትመታቸውን ማሳተም ሲፈቀድላቸው የሱን ግልጽ ባልሆነ መንገድ መከልከል ይበልጥ በህዝብ እይታ እዲገባና ተቀባይነት እንዲያገኝ ረድቶታል።

በግሌ እስክንድርን ሳውቀው እልህኛና ከሱ የተለየ ሃሳብ በጋዜጣው ማስተናገድ የማይሻ ነገር ግን እሱ የሚለው ደጋፊ ሃስብ ለሚይመነጭ በሩ ክፍት መሆኑን በቅርብ አውቃለሁ። ላምነበት ያለው ቁርጠኝነቱም መመስከር እችላልሁ ሙሉ በሙሉ የሚያራምዳቸው ሃሳቦች ባልጋራም። በርግጥ የሌላውንም ሃስብ ቢያስተናግድና ሃሳቦች እንዲፋጩ ዕድል ቢሰጥ ራሱኑም ይበልጥ በማንበብም በውይይትም ቢያጠናክር በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ፖለቲክ አሻራውን ማኖር ይችላል የሚል ዕምነት አለኝ።

የዚህ ጽሁፍ ዓላማ ደጋፊም ተቋዋሚም ማን ምን እንደሆነ ፣ የኃላ ታሪኩን ተመልክቶ ካለው ነባርዊ ሁኔታ በማጣጣም እንድዛፍ ወደነፈሰበት ከመሄድ አውቆና ተርድቶ ያሻውን ቢከተል በዕምነት የተውሰደ ዕርምጃ ራስንም ሌላውንም አስፈላጊ ካልሆነ አውዳሚ ድርጊትና መስዋትዕነት ያድናል። ከዚህም አልፎ ተከታዩን ትውልድ በምክንያትና በውይይት የሚያምን እንዲሆን ይረዳል። የዕድሜ ባለጸጋዎችም ያስልፋቹሁትን ጊዜ ከስኬታቹሁም፤ከውድቀታችሁና ከስህተታቹሁም በመነሳት ቀጣዩ ትውልድ ከዛሬው የተሻለ አስተሳስብና አመለካከት እዲኖረው ማድረግ የትውልድም፣ የታሪክም፣ አደራና የውዴታ ግዴታ እንዳለባቹሁ በመገንዘብ ልትረዱ ይገባል። ጉድጋዱ የተማሰ ልጡ የተራስ ሁሉ እኔ በቃኝ እስኪ እናንተ ደግሞ ከዚህ ቀጥሉ ማለት የግድ ነው። ሥርዓት ቀብርም እኮ የሚያምረው ሀገር ሲኖር ነው።

ወጣቶችም ዛሬ በብዙ መንገድ ከትናንት የተለየ ነው። እንዳለው ነባራዊ ሁኔታ ማስብና የምትረከቡትን ሀገራዊ አደራ ለተከታዮቹ እስከታስተላለፉ ድረስ የራሳቹህ አስትዋጽኦ ማድረግ ይግባቹኃል በትናንት እራት ዛሬ ጾም አይታድረም። ከትናንቱ በጎ በጎውን እያጠናከራቹህ የጎደለውን እይሞላቹህ መጋዝ እንጂ በነብር ታሪክና ሙት በመውቀስ መናቆር ለናንተም ለተከታዩ ትውልድም አይበጅም። ትውልድ ሂደቱን ማስቀጠል ካልቻለ ሀገርም ታሪክም አይኖርም።

እንዲህ ጢሶ ጢሶ የነደደ እንደሆን፣

ያመዱ መፍሰሻ ስፍራው ወዴት ይሆን ከሚለው ይሰውረን